# ዶ/ር መረራ ስለምን “ቀዩን መስመር” አለፉ?

ኢዛና ዘ መንፈስ 12-20-16

ዶክተር መረራ ጉዲናን “የአዲስ አበባው ዳውድ ኢብሳ” እያሉ የሚጠሯቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ፡፡ ሰዎቹ ለምን ግለሰቡን በዚህ ቅፅል ስም እንደሚጠሯቸው ሲጠየቁም፤ ዶክተሩ በሰላማዊ ትግል ሽፋን የሚያራምዱት ፅንፈኛ የፖለቲካ አቋም፤ ኦ.ነ.ግ የሚታወቅበትን የጠባብ ብሔርተኝት አስተሳሰብ የሚያንፀባርቅ ሆኖ ስለሚሰማቸው እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በእርግጥም ደግሞ ሰውየውን ከኦ.ነ.ግ ሊቀ መንበር ከአቶ ዳውድ ኢብሳ የሚለያቸው ምክንያት አለ ከተባለ፤ ምናልባትም እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ እየኖሩ ኢትዮጵያን ለማተራመስ የውጭ ኃይሎች የነደፉትን የሁከትና የብጥብጥ ስትራቴጂ ለማሳካት ያለመ ጉዳይ ስለሚያስፈፅሙ ይሆናል እንጂ ሌላ ትርጉም ያለው የፖለቲካዊ አቋም ልዩነት አይስተዋልባቸውም፡፡

ከዚህ አኳያ በዶክተር መረራ ጉዲና ላይ የሚቀርብባቸው ቅሬታ ምን ያህል ወደተጨባጩ እውነታ የተጠጋ ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ስለሚችል፤ እኔ እንደ አንድ የኢትዮጵያን የተቃውሞ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ከመከታተል ቦዝኖ የማያውቅ ታዛቢ፤ ሰውየው የኦ.ነ.ግ.ን አቋም በሰላማዊ ትግል ሽፋን ለማራመድ ሲሞክሩ ከተስተዋሉባቸው አጋጣሚዎች መካከል አንዱን ብቻ ለአብነት ያህል ላስታውስና ከዚያም ሰሞኑን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ቀይ መስመር አልፈው ስለተገኙበት አጉል ድፍረታቸው ወደማነሳበት ነጥብ አመራለሁ፡፡ ስለዚህም ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት፤ የቀድሞው የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ አገራችን ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ለምትገነባው የህዳሴ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ማኖራቸውን ተከትሎ፤ ያን በምልዓተ ሕዝቡ ዘንድ ለማመን የሚያዳግት አገር አቀፋዊ መነቃቃትን የፈጠረ መልካም ዜና ከተቃወሙት የፖለቲካ ልሂቃን ዶ/ር መረራ ቀዳሚው እንደነበሩ ልብ በሉልኝና ሰውየው ያኔ የኦ.ነ.ግ.ን አቋም ያንፀባረቁበት አግባብ ምን ይመስል እንደነበርም ለአብነት ያህል እጠቅሳለሁ፡፡

እንግዲያውስ ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ በዓባይ ወንዝ ላይ እንደሚገነባ ይፋ የተደረገበት ዜና መደመጡን ተከትሎ፤ የያኔው ኢ.ቴ.ቪ. ጋዜጠኞች ስለ ጉዳዩ አስተያየት ከጠየቋቸው የተቃውሞው ጎራ ፖለቲካ ልሂቃን መካከል አንዱ ዶክተር  መረራ ጉዲና “… እንዴ

ታዲያ የዓባይ ውሃ መገደብ አለመገደብ ጉዳይ እኛን በምን ይመለከተናል?” ሲሉ ጋዜጠኛውን መልሰው ጠየቁና “ባይሆን የዓባይ ልጆች የሆኑትን ተቃዋሚዎች ፈልገህ ብትጠይቃቸው ይሻላል እንጂ እኔ እንኳን በማይመለከተኝ ነገር ውስጥ ገብቼ የምሰጥህ አስተያየት አይኖርም” የሚል ስላቅ መሰል ሃሳብ አክለው ምፀታዊ ሳቅ እየሳቁ ከካሜራው እይታ ለመሸሽ ሲጣደፉም ጭምር የታዘብንበት አጋጣሚ እንደነበር ማስታወስ ይቻላል፡፡

ዶክተሩ ይህን አሳፋሪ የጎጠኝነት አመለካከት የተጠናወተው ምላሽ ሲሰጡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ ሊቀመንበር ነበሩ፡፡ እናም “ታዲያ እኛን በዓባይ ጉዳይ ምን አገባን?” ሲሉ መድረኩ ውስጥ የተካተቱት ብሔራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች “እንወክላቸዋለን” የሚሏቸውን የአገራችን ሕዝቦች ጭምር ጉዳዩ እንደማይመለከታቸው አድርጎ ለማቅረብ ከመፈለግ ኦ.ነ.ጋዊ ከፋፋይ አቋም በመነጨ ስሜት ያንፀባረቁበትን መርዘኛ ፕሮፖጋንዳዊ አንድምታ ያዘለ ንግግር እንደነበረ በወቅቱ አስተያየታቸውን ሲሰጡ ከተደመጡ አንዳንድ ታዛቢዎች ተረድቻለሁ፡፡ እንደምሳሌ መጠቀስ የሚገባው ሆኖ የሚሰማኝ ደግሞ፣ በተለይም የኢፌዴሪ መንግስት የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሚኒስትር የነበሩት አቶ በረከት ስምኦን ከጥቂት ዓመታት በፊት የህዳሴውን ግድብ የግንባታ ሒደት ስለሚቃወሙ ግብፃውያንና የኢትዮጵያ መንግስት ጉዳዩን ስለያዘበት ዲፕሎማሲያዊ አግባብ ለኤፍ ኤም አዲስ 97.1 ሬዲዮ ጣቢያ ጋዜጠኞች በሰጡት ማብራሪያቸው “ምን ሩቅ ሔደን አገራችን በዓባይ ወንዝ ላይ እየገነባች ያለውን የህዳሴ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ በተመለከተ ቅሬታ ስለሚያሰሙ አንዳንድ የግብፅ ዜጎች ጉዳይ እንዲህ ነው እንዲያነው ማለት አስፈለገ? እዚሁ አገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እየመሩ ያሉ የራሳችን ሰዎችም ጭምር የዓባይ ጉዳይ እኛን አይመለከተንም ብለው በሚዲያ ሲናገሩ ተደምጠዋል እኮ” የሚል ሃሳብ ሲሰነዝሩ መስማቴን ነው፡፡ ይህ የአቶ በረከት ንግግር በቀጥታ የሚመለከተው የአዲስ አበባውን “ዳውድ ኢብሳ” ወይም ዶክተር መረራ ጉዲናን ስለመሆኑ ደግሞ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ምክንያቱም ሰውየው አቶ በረከት ስምኦን ለአብነት ያህል በደምሳሳው ያቀረቡትን ሃሳብ በቀድሞው ኢ.ቴ.ቪ. ላይ አሳምረው የገለፁበትን እውነታ በማያሻማ መልኩ ታዝበናልና ነው፡፡

ስለዚህ እንደኔ እምነት ከሆነ፣ መጀመሪያ ላይ “የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረንስ” በምህፃረ ቃል (ኦ.ብ.ኮ) የተሰኘው ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት መስራችና መሪ ስለመሆናቸው

ይነገርላቸው የነበረውና አሁን ደግሞ የእርሳቸው ድርጅት ቀደም ሲል ኦ.ፌ.ዴ.ን አልያም "የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ" ይባል ከነበረው ድርጅት ጋር የተጣመረበትን የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረንስ (ኦ.ፌ.ኮ) የሚባለውን ድርጅት ወክለው የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ እንደሚያካሂዱ ተደርጎ ሲወራላቸው የቆየው ዶክተር መረራ ጉዲና፣ በሕጋዊነት ሽፋን ሥርዓቱን የመናድ ተልዕኮ ለመፈፀምና ለማስፈፀም ቆርጠው ከተነሱት የኦ.ነ.ግ ጀሌዎች መካከል የሚመደቡ ነውጠኛ ግለሰብ ናቸው እንጂ ሌላ ስም አይገልፃቸውም ባይ ነኝ፡፡

ይህን እውነት የሚጠራጠር ሰው ካለም፣ ዶክተሩ ከላይ የከዛሬ አምስት ዓመት በፊት ስለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ በሚያወሳው መልካም ዜና ዙሪያ የሰጡትንና ከላይ የጠቀስኩትን አስተያየት፣ በቅርቡ ከግብፅ ሚዲያዎች ከተገኘው የኦ.ነ.ግ ቃል አቀባይ የአቶ ገመዳ ጪፌ ድርጅታዊ አቋም ጋር ማመሳከር የተሻለ ማረጋገጫ ሊሆን እንደሚችል እጠቁመው ዘንድ እወዳለሁ፡፡ ምክንያቱም፣ መስከረም 22 ቀን 2009 ዓ.ም የተከበረውን የኢሬቻ ዓመታዊ በዓል ተከትሎ በተቀሰቀሰው የሁከትና ብጥብጥ ተግባር የኦሮሚያን ክልል ለማተራመስ ከተሞከረበት አገር አውዳሚ ክስተት በስተጀርባ እጃቸው የነበረበት ኦ.ነ.ግ እና አንዳንድ ፀረ ኢትዮጵያ አቋም በማራመድ የሚታወቁ ግብፃውያን ፖለቲከኞች፣ እዚህ ያሉት ጉዳይ አስፈፃሚዎቻቸው ያቀጣጠሉት የአመፃ እሳት የማይቀለበስ መስሏቸው ኖሮ፣ ካይሮ ውስጥ በተጠራ "የምክክር መድረክ" ተብያቸው ላይ ተሰባስበው የባሰ ጥፋት ሲደግሱልን የተስተዋሉበትን የክህደት ሴራ በተመለከተ አፈትልኮ የወጣውን የግብፅ ሚዲያዎች ምስጢራዊ ዘገባ የኛዎቹ (የአገር ቤት) መገናኛ ብዙሃን ተቀብለው ሲያስደምጡን መሰንበታቸው አይዘነጋምና ነው፡፡

ምናልባት ያ አስነዋሪ ፀረ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሴራ ስለተዶለተበት የካይሮው ምስጢራዊ መድረክ የሚያወሳ ሰሞነኛ ዘገባ የመስማት ዕድል ያልገጠመው አንባቢ ቢኖር ግን "… እናንተ ግብፃውያን የትግል አጋሮቻችን የተለመደ ድጋፋችሁን የበለጠ አጠናክራችሁ እስከቀጠላችሁና ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲም የኢትዮጵያን መንግስት ለማስወገድ የሚያስችለንን እገዛ እንዲያደርጉልን እስካሳመናችሁልን ድረስ እኛ አሸንፈን ስልጣን ከያዝን በሁዋላ የህዳሴውን ግድብ ግንባታ እናስቆማለን" ሲል ነው ኦ.ነ.ግ በቃል አቀባዩ በኩል ቃል የገባው፡፡ እነርሱ የመንግስትነት ስልጣኑን ጨብጠው ወደ አራት ኪሎው ቤተ መንግስት የመግባት ዕድል ይገጠማቸው እንጂ የዓባይ ተፋሰስን የውሃ ሀብት ለኢትዮጵያና

ለኢትዮጵያዊያን ሕዝቦች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የማዋል ጉዳይ እንደ አጀንዳ ሊነሳ የማይችልበትን "ዘላቂ መላ መምታት እንደማያቅታቸው" ጭምርም ነው የኦ.ነ.ግ ቃል አቀባይ አቶ ገመዳ ጪፌ ለግብፃውያኑ የነውጥ ፖለቲካ ሸሪኮቻቸው ያረጋገጡት፤

እናም በእኔ እምነት፤ ዶክተር መረራ ጉዲና ለምን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ላይ የተቀመጠውን ቀይ መስመር ጥሰው በማለፍ ወደ አውሮፓዊቷ ሀገር ቤልጂየም ለመሔድና በሽብርተኝነት የተፈረጀውን "ግንቦት ሰባት" የተሰኘ ቡድን ከሚመራው ከዶክተር ብርሃኑ ነጋ ጋር ተገናኝተው ለመዶለት ፈለጉ? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያን ያህልም ከባድ ሆኖ አይሰማኝም፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ዶክተር መረራ፤ ይህን አጉል ድፍረት ለመፈፀም የተገፋፉት ያው ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው "የአዲስ አበባው ዳውድ ኢብሳ" ለመባል ያበቃቸውን የኦ.ነ.ግ.ነት አስተሳሰብ ተግባራዊ የማድረግ ተልዕኮ አንግበው የሚንቀሳቀሱ የፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ጉዳይ አስፈፃሚ ግለሰብ እንጂ በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የሚያምኑ አይደሉምና ነው፡፡

ደግሞስ እውነቱን መነጋገር ካለብን፤ እርሳቸውና ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ፋይዳቢስነት ለአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ጣቢያ (ቪ.ኦ.ኤ) የአማርኛው ክፍል ሲናገሩ የሰማነው ገና የአዋጁ መደንገግ ይፋ መሆኑን ተከትሎ አልነበረም እንዴ? ማለትም፤ ዶክተር መረራ ጉዲና ራሳቸው ከአንድ ወር በፊት "የኢህአዴግ መንግስት ለምን ጉዳዩን እንደ አዲስ ነገር በአዋጅ መልክ ሊያወጣው እንደፈለገ እንጃ እንጂ ለኛ ለተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን አሁን የሚባለው ሁሉ ተግባራዊ ሲደረግ የነበረና ምንም ዓይነት ከእስከዛሬው የተለየ ተአምር ሊፈጥር እንደማይችል ሆኖ ነው የሚሰማን" ሲሉ ተደምጠዋል እኮ ለቪ.ኦ.ኤ በሰጡት ወቅታዊ ቃለ ምልልስ፤ ታዲያ ሰውየው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በእርግጥም ፋይዳ ቢስ ተደርጎ እንዲወሰድላቸው ሲሉ "በሽብረተኝነት ተግባር ላይ ተሰማርተው ማንኛውንም ዓይነት ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴ ከሚያደርጉ ቡድኖችም ሆነ ግለሰቦች ጋር ግንኙነት መፍጠር የተከለከለ ነው" የሚለውን ድንጋጌ ጥሰው ከዶክተር ብርሃኑ ነጋ ጋር የዛሬዋን ኢትዮጵያ እንደ አገር ስለማተራመስ ጉዳይ ሊመክሩ ወደ ቤልጂየም ብራስልስ ቢያቀኑ ምን ያስገርማል? እንግዲህ ዶክተሩ ይሆነኝ ብለው የኦ.ነ.ግ. ጀሌነትን እንደ አርበኝነት ከቆጠሩትና ነውጠኝነት ከመረጡ፤ ብሎም "ቀይ መስመሩ"ን ካለፉ "ስራህ ያውጣህ" ነው እንጂ ሌላ ምን ይባላል!? **አበቃሁ!**